የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት
ልሣነ- ሕግ ጋዜጣ
LISAN HIG GAZETA
OF THE BENISHANGUL — GUMUZ REGIONAL STATE
የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት
ም/ቤት ጠባቂነት የወጣ

17 ኛ ዓመት ቁጥር 51 አሶሳ
ሐምሌ 1997

17th Year No 51
Assosa July 2005

**አዋጅ ቁጥር 51/1997 ዓ.ም**

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊመንግስት ሰንደቅ ዓላማና ዓርማ አዋጅ

የተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ሕገ-መንግስት ክልሉ የራሱ ዓላማና ዓርማ እንዲኖረው በመደንገጉ፤

ለሕገ-መንግስቱ ድንጋጌዎች አፈጻጸም ሰንደቅ ዓላማና ዓርማ የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮች የሚወስን አዋጅ ማወጅ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት አንቀጽ ፵፱ /፫/ / ፩ / እና አንቀጽ ፬/ ፪/ መሠረት የሚከተለው ታወጇል፡፡

PROCLAMATION NO 51/2005

BENISHANGUL GUMUZ REGIONAL STATE FLAGE AND EMBELEM PROCLAMATION

WHEREAS, the Revised Constitution of Benishangul Gumuz Regional State provided that the Region shall have its own Flag and Emblem;

WHEREAS, in consequence thereof, it is found necessary to promulgate a Proclamation deterring particulars on Flag and Emblem;

NOW, THEREFORE, in accordance with Articles 49(3) (1) and 4(2) of the Revised Constitution of Benishangul Gumuz Regional State, it is hereby proclaimed as follows.

**ክፍል አንድ**

**<u>ጠቅላላ</u>**

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ሰንደቅ ዓላማ እና ዓርማ አዋጅ ቁጥር ፶፩/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**<u>ክፍፀልፀ ሁለት</u>**

**<u>ስለሰንደቀለማና ዓርማ</u>**

**፪. <u>የሰንደቅ ዓላማው ትርጓሜ</u>**

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ሰንደቅ ዓላማ ከዚህ በኂላ "ሰንደቅ ዓላማው" እየተባለ የሚጠራ የክልሉ ብሔረሰቦችና ሌሎች ሕዝቦችን በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ አንድነት መግለጫ ነው፡፡

**፫. <u>የሰንደቅ ዓላማው ቀለማትና ቅርጽ</u>**

፩ ሰንደቅ አላማው ከላይ ጥቁር ከታች አረንጓዴና ከመሀል ቢጫ በሰንደቁ በኩል ሁሉንም ቀለማት የሚነካ ሶሶት መህዘን ቀይ ያለበት ሆኖ ዙሪያው ነጭ ፍሬም ያለው ይሆናል፡፡

፪ ቀለማቱ ብሩህና መሠረታዊ ይሆናሉ፡፡ የሰንደቅ ዓላማውን መውለብለብ የሚያግድ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመው በስተቀር፣

፫ የጥቁር፣የቢጫና የአረንጓዴ ቀለማቱ አግድም የተሰመሩና እኩል ስፋት የሚኖራቸው ይሆናሉ፡፡

፬ ቀዩ በሰንደቁ በኩል ሁሉንም ቀለማት የሚነካ ባለ ሶስት ማእዘን በቢጫው መደብ መሀል ላይ ሾጠጥ ብሎ ያርፋል፡፡

፭ የሰንደቅ አላማው ወርድ የቁመቱ እጥፍ ይሆናል፡፡

**PART ONE**

**General**

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as "The Benishangul Gumuz Regional State Flag and Emblem Proclamation No.51/2005."

**Part Two**

**Flag and Emblem**

2 **Symbolism of the Flag**

The Flag of Benishangul Gumuz Regional State, hereafter << the Flag >>symbolizes the unit based on the consent of Nationalities and other peoples of the Region.

**3. Colors and Shape of the Flag**

1. The Flag shall have colors black at the top, green at the bottom and yellow in the middle and triangular with red color that touches all colors on the side of the flagstaff and its perimeter shall have white frame.
2. The colors shall be bright and basic.
3. The black, yellow and green colors shall be horizontally structured and shall have equal area.
4. The triangular with red color that touches all colors at side of the flagstaff shall sharply be placed in the middle of yellow ground.
5. The length of the Flag shall be twice its width.

**፬. <u>የሰንደቅ ዓላማው ቀለማት ትርጉም</u>**

፩ የሰንደቅ አላማው ቀለማት የሚከተለው ትርጉም ይኖራቸዋል፡፡

ሀ/ ጥቁሩ፡- የብሄረሰቦቹን መልክ፣


ለ/ ቢጫው፡- የተስፋ፣የፍትሕና የእኩልነት ምልክት፣

ሐ/ አረንጓዴ፡- የልምላሜና የዕድገት ምልክት፣

መ/ ቀዩ፡- ለክልሉ ነጻነትና ፍትህ፣ለልማትና ሰላም የተከፈለ መስዋዕትነት ምልክት፣

ሠ/ ነጩ ፍሬም፡-ክልሉ ከአጐባች መንግስታት፣ የክልሉ ብሔረሰቦች ከሌሎች ብሄር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ጋር የሚኖራቸው የመልካም ግንኙነትና ሰላም ምልክት ነው፡፡

**፭. <u>የሰንደቅ ዓላማው ስዕላዊ መግለጫና አቀማመጥ</u>**



**፮. <u>የሰንደቅ ዓላማው አወጣጥ</u>**

የሰንደቅ ዓላማውን መውለብለብ የሚያግድ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመው በስተቀር፣

**4. Meaning of the Colors of the Flag**

1 The colors of the Flag shall represent the following meanings;

a) The black: for appearance of the Nationalities,


b) The yellow: for hope, justice and equality,

c) The green: for fertility and development,

d) The red for sacrifice paid for freedom and justice, development and peace of the Regional,

e) The white frame: for the existence of good relationship and peace between the Region and other neighboring Regions, the Nationalities of the Region and Nations and Nationalities and peoples of other Regions.

**5. Pictorial Representation and Position of the Flag**



**6. Display of the Flag**

Except in cases of forces majeure obstructive to having it flows:

1 በክልል ም/ቤት፣በመስተዳድር ም/ቤት፣ በጠቅላይ ፍ/ቤት፣በዋናው ኦዲተር መ/ቤት፣በሁሉም የክልሉ የተዋረድ መንግስታዊ ተቋማት / አስፈጻሚ መ/ቤት ጽ/ቤቶች፣ት/ቤቶች/ ፣ በፖሊስና በሌሎች የጥበቃ ጽ/ቤቶች በክልላዊ መንግስቱ ቤተ-መንግስት ሰንደቅ ዓላማው በየቀኑ ይውለበለባል፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ያልተመለከቱ የክልሉ መንግስት መ/ቤቶችና ሌሎች በክልሉ የሚገኙ የፌዴራል መንግስት ተቋማት እንዲሁም ድርጅቶች/ማኅበራት በብሔራዊና በክልላዊ በዓላት የክልሉን ሰንደቅ ዓላማ ያውለበልባሉ፡፡

## ፯. የሰንደቅ ዓላማው መጠን

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫/፭ የጠቀሰው እንደተጠጠበቀ ሆኖ ሰንደቅ ዓላማው የሚከተለው መጠን ይኖረዋል፡፡

፩ በከፍተኛ አደባባይ የሰንደቅ ዓላማ መጠን 210 x 420 ሴ.ሜትርና የሰንደቁ ቁመት ከ15-18 ሜትር፣

፪ በመካከለኛ አደባባይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን 150 x 300 ሴ.ሜትርና የሰንደቁ ቁመት 10-15 ሜትር፣

3 በመ/ቤቶች፣በከፍተኛ የትምህርት ተቋሞችና ድርጅቶች አደባባይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን 135x270 ሴ.ሜትርና የሰንደቁ ቁመት 10-12 ሜትር፣

1. The Flag shall fly daily at the Regional State Council, the Administrative Council, the Supreme Court, the Office of Auditor General, at all levels of subsequent of governmental institution (executive offices, schools), the offices of police and other guards, parks of the Regional Government.
2. Government offices that are not specified under sub article 1 of this Article and other Federal Government institutions as well as establishments /cooperative that are found in the Region shall fly the Flag at the National and Regional holidays.

## 7. Size of the Flag

Without prejudice to the stipulation of Article 3(5) of this Proclamation, the Flag shall have the following size.

1) At major squares, the size of the Flag shall be 210 by 420 cm. and the Flagstaff shall be from 15 to 18 meters high,

2.) At medium squares, the size of the Flag shall be 150 by 300 cm. and the Flag staff shall be from 10 to 15 meters high,

3) At the squares of offices higher educational institutions, and establishments, the size of the Flag shall be 135 by 270 cm, and the Flagstaff shall be from 10 to 12 meters high,

4 በትልቅቅ የመንግስት ሕንፃዎች ላይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን 135x270 ሴ.ሜትርና የሰንደቁ ቁመት 5 ሜትር፣

5 በትልልቅ ሕንፃዎች ምድር ቤት ውስጥ የሚገኙ ድርድቶችና የንግድ ቤቶች የሰንደቅዓላማው መጠን 105 x 210 ሴ.ሜትርና የሰንደቁ ቁመት 3 ሜትር፣

6 በሰልፍ ጊዜ በክብር ዘብ የሚያዘው የሰንደቅ ዓላማ መጠን 105 x 210 ሴ.ሜትርና የሰንደቁ ቁመት 230 ሴንቲ ሜትር፣

7 ለፌዴራልም ሆነ ለውጭ ሀገር እንግዳ አቀባበልና ለበዓላት በየመንገዱ ለሚውለበሰብ የሰንደቅ ዓላማ መጠን 90 x 180 ሴ.ሜትርና የሰንደቁ ቁመት 2 ሜትር፣ወይም የካቢኔ አባላት ጽ/ቤት ጠረጴዛ ላይ የሰንደቅ ዓላማ መጠን 21 x 42 ሴ.ሜትርና የሰንደቁ ቁመት 30ሴ. ሜትር ሆኖ ይዘጋጃል፡፡

8 በክልሉ ኘሬዚዳንት፣ በርዕሰ መስተዳድሩ እና በምክትሉ፣በአፈ-ጉባዔና በምክትሉ፣ በጠቅላይ ፍ/ቤት ኘሬዚዳንትና በምክትሉ፣በዋና ኦዲተርና ምክትሉ እና በሌሎች የመስተዳድር ም/ቤቱ የሰንደቅ ዓላማ መጠን 21 x 42 ሴ.ሜትርና የሰንደቁ ቁመት 5 ሴንቲ ሜትርሆኖ ይዘጋጃል፡፡

8 <u>የሰንደቅ ዓላማው መትከያ ስፍራ</u>

በአደባባይ የሚወለበለብ የሰንደቅ ዓላማ የሚተከለው በተቻለ መጠን ከመስሪያ ቤቱ ህንፃ ፊትለፊትና መሀልለማሀል ይሆናል፡፡

4) On major government buildings, the size of the Flag shall be 135 by 270 cm. and the Flagstaff shall be 5 meters high,

5) At organizations and business enterprises in the ground floor of major buildings, the size of the Flag shall be 135 by 270, and the Flag staff shall be 3 meters high,

6) When displayed by a guard of honor in procession, the size of the Flag shall be 105 by 210 cm and the Flagstaff shall be 230 cm,

7) In honor of federal and foreign guests and on public holidays, the size of the Flag flown in streets shall be 90 by 180 cm. and the Flag staff shall be 2 meters high,

8) On the desks of the office of the president, chief executive and the vice, speaker, and the vice, president of Supreme Court and other offices of administrative council or carbine members, the size of the Flag shall be 21 by 42 cm, and the Flagstaff shall be 5 cm high.

**8. <u>Place for setting up the Flagstaff</u>**

The flagstaff of the Flag flown at square shall, as far as possible, be set up at the center in the front of the Office building.

**፱. <u>የሰንደቅ ልሳን</u>**

የማንኛውም ሰንደቅ ጫፍ የጦር አምሳል ይኖረዋል፡፡

**፲. <u>ሰንደቅ ዓላማው የሚወጣበትና የሚወርድበት ጊዜ</u>**

፩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና ፭ የመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰/፩/ የተጠቀሱት መ/ቤቶች ከጧቱ 12፡00 /ሰዓት/ ወጥቶ ከምሽቱ 12፡00 /ሰዓት/ ይወርዳል፡፡ሆኖም የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ በታወጀበት አካባቢዎች የሚገኙ የመከላከያና የፖሊስ ሠራዊት አሀዶች ሁኔታው እስካልተለወጠ ድረስ መደበኛውን ሰዓት ጠብቀው ሰንደቅ ዓላማውን ማውጣትና ማውረድ አይገደዱም፡፡

፪ በትምህርት ቤቶች ሰንደቅ ዓላማው የሚወጣው ጠዋት ተማሪዎች ተሰልፈው ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ይሆናል፣፣

፫ በበዓል ቀናት ሰንደቅ ዓላማው በዋዜማው ወጥቶ በበዓሉ ማግስት ይወርዳል፡፡

፬ የክልሉ ሰንደቅ ዓላማ ከፌዴራሉ ሰንደቅ ዓላማበተጓዳኝዘወትር ይወጣል፣ይወርዳል፡፡

፲፩. በክልሉ የሚገኝ ማንኛውም ሰው ይህንን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ሰንደቅ ዓላማ የሚገባውን ክብር የመስጠትና የማክበር ኃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡

**9. <u>Tip of the Flag staff</u>**

The tip of any Flagstaff shall be spear headed.

**10. Time of Hosting and Lowering of the Flag**

1) Without prejudice to sub article 2 and 5 of this Article, Flag shall be hosted at 6am and lowered at 6 pm at offices specified in Article 8(1) of this Proclamation. However, military units in regions where a state of emergency has been declared need not comply with the regular hosting and lowering time until the situation changes.

2) In schools, the Flag shall be hosted in the morning before classes begin and lowered after the day's classes end, hosting and lowering shall take place at a procession ceremony of students.

3) The Flag shall be hosted on the eve and lowered on the morrow of public holidays.

4) The Flag of the Region shall always host and lowered parallel to the Flag of the federal.

**11.** Any person in the Region shall have the responsibility and duty to pay due honor to the Flag of Benishangul Gumuz Regional state

## ፲፪. <u>የዓርማው ስዕላዊ መግለጫና አቀማመጥ</u>



## ፲፫. <u>የዓርማው ትርጉም</u>

1 የክልሉ ዓርማ ቅርጽ ክብና የውስጥ ዙሪያው በቀርቀሃ የተከበበ፣በመሀሉ ሚዛን ሆኖ፣ከሚዛኑ ሥር ወርቅ የያዘ ገበታ እና ቀርቀሃው ያረፈበት የማሽን ጥርስ ያለው ይሆናል፡፡

2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ / ፩/ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

ሀ/ ቀርቀሃው በክልሉ ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት ክምችት መኖሩን የሚያመላክት ነው፡፡

ለ/ ሚዛኑ በክልሉ ፍትሕና እኩልነትን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ትግል የሚወክልነው፡፡

ሐ/ ወርቅ የያዘው ገበታ በክልሉ ሊመረቱ የሚችሉ ከፍተኛ የከበሩ ማዕድናት ያሉ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡

መ/ የማሽኑ ጥርስ የክልሉን በኢንዱስትሪ የመበልጸግ ተስፋን የሚወክል ነው፡፡

## 12. Pictorial Representation of the Emblem



## 13. Meaning of the Emblem

1. The Emblem of the Region shall have circle shape and its internal parameter surrounded by bamboo, scale in the centre, a dish having gold at the bottom of the scale, and a machine gear on which the bamboo based.
2. Without prejudice to sub article 1 of this Article:
   a) The bamboo symbolizes the high concentration of natural resources in the Region,
   b) The scale symbolizes the effort to be made to ensure justice and equality in the Region,
   c) A dish with gold symbolizes the existence of potential production of precious minerals in the Region,
   d) The machine gear symbolizes the hope of industrial prosperous of the Region.

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፬. ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ይህንን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆነ ደንብ ለማውጣት ይችላል፡፡

፲፭. በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ተከትሎ በክልሉ የሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት የአፈጻጸም መመሪያዎችን ለማውጣት ይችላሉ፡፡

**፲፮. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ይህንን አዋጅ የሚቃረን አዋጅ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፲፯. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፯ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ሰኔ ፯ /፲፱፻፺፯ ዓ.ም**

**አሶሳ**

**ያረጋል አይሸሽም**

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት**

**ፕሬዚዳንት**

## PART THREE

## Miscellaneous Provisions

**14. The Power to Issue Regulation**

The Administrative Council of the Region may issue a Regulation necessary to enforce this Proclamation.

**15.** The concerned government organ of the Region may, based on the Regulation to be issued pursuant to Article 14 of this Proclamation, issue procedural/executive directives.

**16. Inapplicable Laws**

Any Proclamation or customary practice that contravenes this Proclamation shall not be effective on matters that fall under this Proclamation

**17. Effective Date**

This Proclamation shall be effective since August 13, 2005.

**Done at Assosa, August 13/2005**

**Yaregal Aysheshim Birhane**

**The President of Benishangul Gumuz**

**Regional State**